የሰ/መ/ቁ. 36518

ጥቅምት 4 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- ሜታ አቦ ቢራ አክሲዮን ማህበር - አልቀረቡም፡፡

**ተጠሪ**፡- እነ ሳሙኤል ተፈራ (4 ሰዎች) - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ ሕግ መሰረት የሚታይ ክርክር ሆኖ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ተከሣሽ ተጠሪዎች ከሣሾች ነበሩ፡፡ ተጠሪዎች አመልካችን የከሰሱት በድርጅቱ ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ የሕክምና ሰራተኞች መሆናቸውን ገልፀው ከጽሁፍ ሥራ ጋር በተያያዘ የተቋረጠባቸውን ክፍያ፣ በሽፍት ለሰሩት ሥራ ሊከፍል የሚገባውን ክፍያ እና የአልጋ ክፍያ እንዲከፍላቸው እንዲሁም የጽዳት ሰራተኛ እንዲመድብላቸው በመጠየቅ ነው፡፡

አመልካችም ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ አመልካች ቢራ አምርቶ ለመሸጥ የተቋቋመ ድርጅት ነው፤ ተጠሪዎችም ስራቸው የመጀመሪያ የህክምና እርዳታ መስጠት ነው፤ ድርጅቱ ባወጣው የፈረቃ ድልደላ መሰረት እሁድ ስራ ላይ ለዋለ ሰራተኛ በቀጣዩ ቀን 24 ሰዓት እረፍት ይሰጠዋል፤ በሣምንት 48 ሰዓት ይሰራሉ፤ ላልሰሩበት የትርፍ ሰዓት ክፍያ ሊጠይቁ አይገባም፤ በሽፍት ሥራ ለሚሰራ ሰራተኛ የአልጋም ሆነ የእራት ክፍያ የሚፈጸምበት ህጋዊ ምክንያት የለም፤ የሕክምና መሣሪያቸውን የማጽዳት ሐላፊነት የተጠሪዎች ስለሆነ የጽዳት ሰራተኛ ልመድብላቸው አይገባም፤ በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም ክርክሩን መርምሮ ተጠሪዎች በሣምንት 48 ሰዓት እንደሚሰሩ እና እሁድ ቀን በሥራ ላይ ከተገኙ በሚቀጥለው ቀን 24 ሰዓት የሚያርፉ መሆናቸውን በመረዳት ተጠሪዎች በሣምንት 48 ሰዓት ብቻ መስራታቸው እየታወቀ በሽፍት ሥራ እንሰራለን በማለት ብቻ ያቀረቡት የክፍያ ጥያቄ እና የጽዳት ሰራተኛ ይመደብልን ጥያቄ የሕግ ድጋፍ የለውም ውድቅ ነው ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ባለመስማማታቸው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ተከራክረዋል፡፡

የከፍተኛ ፍ/ቤቱም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 61/1/ መሰረት የማንኛውም ሰራተኛ የስራ ሰዓት በቀን ከስምንት ወይም በሣምንት ከ48 ሰዓት አይበልጥም ስለሚል እና የተጠሪዎች ቅሬታ በሣምንት ከ48 ሰዓት በላይ ሰራን ሣይሆን በቀን 16 ሰዓት ሰራን ነው ስለዚህ እንደሰራተኛ በቀን ከ8 ሰዓት በላይ መሥራት ግዴታ ባለመሆኑ አመልካች ተጠሪዎች በቀን 8 ሰዓት ብቻ እንዲሰሩ የሥራ ጊዜውን ያመቻች በማለት በማሻሻል ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ላይ ነው፡፡

አመልካች በጥር 22 ቀን 2000 ዓ.ም በዓፈው ማመልከቻ በከፍተኛው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ይህ የሰበር ችሎትም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል፡፡

ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በከፍተኛው ፍ/ቤት ለተጠሪዎች የሥራ ሰዓት ይመቻችላቸው በማለት የመወሰኑን አግባብነት ከአዋጁ እና ከሕብረት ስምምነቱ አኳያ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረት ይህን ነጥብ ግራ ቀኙ ወገኖች ካሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እኛም የጉዳዩን አመጣጥ ስናየው ተጠሪዎች በአመልካች ድርጅት ሲሰሩ ድርጅቱ ባወጣው የሥራ ሽፍት መሰረት ተስማምተው ሲሰሩ የቆዩ እና በድልድሉ መሰረት እሁድ ቀን ከሰሩ በሚቀጥለው 24፡00 ሰዓት እንደሚያርፉ ተገንዝበናል፡፡ አንድ ድርጅት እንደስራው ፀባይ በሕግ ከተደነገገው ማእቀፍ ሳይወጣ (ሳይጥስ) የሥራ ሰዓቱን ለማሻሻል የሚከለክለው ሕግ የለም፡፡ ተጠሪዎችም በዚሁ ተስማምተው በሣምንት ከ48 ሰዓት በማይበልጥ መልኩ በሽፍት ሲያገለግሉ ቆይተው የሌላቸውን (ያልሰሩበትን) የትርፍ ሰዓት ክፍያ የሚጠይቁበት የሕግ ድጋፍ የላቸውም፡፡ ሌላው የጽዳት ሰራተኛ እንዲመደብላቸው የጠየቁትንም በሚመለከት ቀድሞውኑም ተጠሪዎች የህክምና ባለሙያ በመሆናቸው የራሳቸውን የሕክምና መሣሪያ ሌላ ሰው ያጽዳልን ማለታቸው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ስለዚህ የሰራተኛ ምደባው ውድቅ ነው፡፡

ባጠቃላይ ተጠሪዎች በሕጉ አግባብ በአመልካች ድርጅት እንደሚሰሩ ግልጽ ሆኖ ሳለ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የድርጅቱን የስራ ፀባይ ግምት ውስጥ ሳያስገባ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 61(1) ለመባል ከፈለገው አላማ ጋር በቅጡ ሳያገናዝብ የድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴ በሚገድብ መልኩ በሣምንት ተጠሪዎች 48 ሰዓት መሥራታቸውን እየገለፀ ከአዋጁ መንፈስ ውጭ 8 ሰዓት ብቻ ለተጠሪ ይመቻችላቸው ብሎ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በማሻሻል መወሰኑ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 11276 በቀን ሰኔ 4 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57620 በጥር 22 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡ ተጠሪዎች ምንም አይነት ክፍያ ሊጠይቁ አይገባም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ኪሳራ ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ